# የአጼ ዘርዓ ያዕቆብ “መጽሐፈ ብርሃን” የያዛቸው ሃሳቦች

ዳዊት ግርማ[1]

## አህጽሮተ ጥናት

የመካከለኛው ዘመን ታሪክ በኢትዮጵያ መዝገበ-ታሪክ ውስጥ ወሳኝ ሃገራዊ ኩነቶች የተመዘገቡበት ዘመን ነው። በተለይ በሥነ ጽሑፍ መስክ ከፍተኛ የወጥ እና ትርጉም ስራዎች እድገት የታዬ ሲሆን ከዚህ የታሪክ ዘመን ውስጥም 15ኛው ክ/ዘመን የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ላይ የደረሰበት ጊዜ ነው፡፡ ስለሆነም "ወርቃማው የሥነጽሑፍ ዘመን" ተብሎ ይታወቃል። በዚህ ዘመን በርካታ የታሪክ፣ የፍልስፍና፣ የሃይማኖት፣ የሕግ፣ የዜማ፣ የቁጥር፣ የሰዋስውና የሥነ ፈለክ ይዘት ያላቸው መጻሕፍት ተደርሰዋል። በዘመኑ ከሚጠቀሱ ስመጥር ደራስያን መካከል አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ አፄ ዘርዐ ያዕቆብ፣ ርቱዓ ሃይማኖት፣ አባ ሰላማ፣ አባ ዕንባቆም፣ አባ ሚካኤል፣ ቄስ ሐጼ ዘካርያስ፣ መ/ር ኢሳያስ ግብፃዊ፣ አባ በኃይለማርያም ይገኙበታል። ንጉሥና ደራሲ የነበረው አፄ ዘርዐ ያዕቆብ እንደመፅሐፈ ብርሃን፣ መፅሐፈ ሚላድ፣ እግዚአብሔር ነግሠ፣ መፅሐፈ ባህርይ፣ ጦማረ ትስብእት፣ ራእየ ተአምር፣ ክህዶተ ሰይጣን፣ ስብሐተ ፍቁር ያሉ ከአስር የሚልቁ መጻሕፍትን ፅፏል። ከእነዚህም አንዱ የሆነው መፅሐፈ ብርሃን ነው። መጽሐፈ ብርሃን ከንጉሡ ድርሰቶች ውስጥ ዝነኛው ሲሆን በይዘቱም ሰፊና የ15ኛው መ/ክ/ዘመንን የፖለቲካ ታሪክ የያዘ ነው። ሃይማኖታዊ ጭብጡ ያመዘነ ቢመስልም የታሪክ፣ ማህበራዊ፣ የፖለቲካ እንዲሁም የመንግስት አስተዳደር ብልሃት ሃሳቦችን ያነገበ ነው። መጽሐፉ የመካከለኛው ዘመን በተለይም የ15ኛው ክፍለዘመን ኢትዮጵያን ነባራዊ አውድ ለመረዳት ሁነኛ ሰነድ ነው። ጥናቱ አይነታዊ የጥናት ዘዴን የተከተለ ሲሆን በዘመኑ የነበሩ አብርሆታዊ ንቅናቄዎችን፣ የእውቀት-ርቀት የልሂቀት ማዕከላትን፣ የህዳሴ ሃሳቦችን፣ የባህልና የሃይማኖት መስተጋብሮችን፣ የማህበራዊና የሥነ-ትምህርት አቅጣጫዎችን እንዲሁም አሰላሳይ ሰብዓትን ይዳስሳል።

**ቁልፍ ቃላት፡-** መጽሐፈ ብርሃን፤ ወርቃማው ዘመን፤ ሃዲስ ታሪካዊነት፤ የግእዝ ሥነጽሑፍ

## 1. መግቢያ

የሥነ ጽሑፍ ሥራ በኢትዮጵያ የምዕተ ዓመታት ታሪክ አለው፡፡ የራሳቸው ስርዓተ ጽሑፍ ካላቸው የጥንታዊ ስልጣኔ መገኛ ሃገራት ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ናት፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ የግእዝ ቋንቋ ከሁለት ሺህ ዓመታት በላይ እድሜ ያስቆጠረ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ነው፡፡ የሃገራችን ሊቃውንት ክፍላተ ዘመናትን ያስቆጠሩ ድርሳናትን ጽፈዋል፡፡ በጥንታዊውና መካከለኛው ዘመን የተጻፉ፤ ከድንጋይ ላይ ጽሑፎች እስከ ብራና ላይ ጽሑፋች፤ በትርጉም እና በወጥ በርካታ ድርሳናት ተደርሰዋል፡፡ በጥንት ዘመን የግእዝ ሥነ ጽሑፍ በጠንካራና ለስላሳ ቁሶች ላይ ይሰፍር ነበር፡፡ ጠንካራ ቁሶች የምንለው እንደ ድንጋይ ባሉት (እንጨት፣ ቅርፊትና መሰሎችንም

[1] በአ/አ/ዩ የሥነ ጽሑፍ 3ኛ ዲግሪ ተማሪ፡፡ ኢሜይል፡- dawitzion2000@gmail.com

ይጨምራል)፡፡ የድንጋይ ላይ የግእዝ ጽሑፍ በአክሱም አካባቢ- የነገሥታቱን የዘመቻ ታሪኮችና መሰል ዘገባዎችን ይይዝ ነበር፡፡ በኋላም በተለይ ድኅረ ልደተ ክርስቶስ ከ6ኛው ክ/ዘመን በኋላ በብራና ላይ መጻፍ ጀምሯል፡፡ የብራና ላይ የግእዝ ጽሑፍ ከ6ኛው ክ/ዘመን ጀምሮ የነበረ ተግባር በመሆኑም 1500 ዘመን ያክል አስቆጥሯል፡፡ ጥንታዊው የሚባለው የብራና የግእዝ መጽሐፍ በእንዳ አባ ገሪማ የሚገኘው ወንጌል ሲሆን የተጻፈውም በ6ኛው መ/ክ/ዘ ነው፡፡ እንደ ጌታቸው ኃይሌ በ6ኛው ክ/ዘመን የተነሳው ቅዱስ ያሬድ የግእዝ ሥነ ጽሑፍ መስራች ነው (ጌታቸው፣ 1999)፡፡

የግእዝ ሥነ ጽሑፍ በሁለት መንገድ ይቀርባል፡፡ የመጀመሪያው ትርጉም ሲሆን ሌው ደግሞ ወጥ ነው፡፡ ይህም ማለት ከውጭ ክርስቲያን ሃገሮች ቋንቋዎች ላይ ወደ ግእዝ የተተረጎሙ እና በሃገር ውስጥ ሊቃውንት የተደረሱ ወጥ ጽሑፎች ናቸው፡፡ የትርጉም ስራ በጥንታዊው ዘመን የተለመደ ተግባር ነበር፤ በመካከለኛው ዘመንም ቀጥሏል፡፡ ከጥንታዊ ዘመን የወጥ ሥነ ጽሑፍ ስራ ውስጥ ቅዱስ ያሬድ ይጠቀሳል፡፡ ቅዱስ ያሬድ ከብሉያት፣ ከሐዲሳት፣ ከሊቃዉንት ትምህርቶች እያጣቀሰ ድርሰቶቹን ጽፏል፡፡ በተለይ በድርሰቶቹ ውስጥ የሚንጸባረቁት የቃላት አመራረጥ፣ የዓረፍተ ነገር አሰካከና አወቃቀር እና የዘይቤ አጠቃቀም ለሥነ ጽሑፍ ጥናትም ፋይዳው የጎላ ሆኖ ቅዱስ ያሬድ የሥነ ጽሑፍ ተሰጥኦውም ከፍተኛ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቅዱስ ያሬድ አምስት የዜማ መጻሕፍትን (ድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ዝማሬ፣ መዋስዕትና ምዕራፍ) ደርሷል፡፡ ከቅዱስ ያሬድ ቀጥሎ ወጥ የጽሑፍ ስራዎች በተደራጀ ሁኔታ የተስፋፉት በመካለኛው ዘመን ነው፡፡ የመካከለኛው ዘመን የግእዝ ሥነ ጽሑፍ የእድገት ዘመን ነበር፡፡ ገድሎች፣ ድርሳናት፣ ተአምራት፣ መልክእ፣ ዜና መዋዕላት እና ቅኔን የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ዘውጎች ናቸው (Adamu and Belaynesh, 1970)፡፡

ይህ ጥናት የዐጼ ዘርዐ ያዕቆብ የሥነ ጽሑፍ ስራ የሆነውን መጽሐፈ ብርሃንን ይቃኛል፡፡ ወዲያውም ንጉሡ በዘመናቸው ላበበው የሥነ ጽሑፍ እድገት የነበራቸው ንግለሰባዊ ጥረት፣ አበርክቶትና ሱታፌ ይዳስሳል፡፡ ንጉሡ በርካታ መጻሕፍትን ደርሰዋል፡፡ ዐጼ ዘርዐ ያዕቆብ ሊቃውንትንና ጠቢባንን በቤተመንግስቱ አሰባስቦና አንድ የተለዬ ቦታ ወስኖ ቀለብ እየሰፈረ እንዲጽፉ፣ እንዲመራመሩ፣ እንዲራቀቁ እና ሥነጽሑፋዊ እንቅስቃሴውን በይፋ እንዲያበረቱ ያደርግ ነበር፡፡ እንደአባጊዮርጊስ ዘጋስጫ ያሉ ሊቃውንት አያሌ መጻሕፍትን የደረሱ ሲሆን መጽሐፍቱም ኃይማኖታዊ ከመሆናቸው ባሻገር ለሥነ ጽሑፉ እሴት የጨመሩ ናቸው፡፡ ንጉሡ ከአስር በላይ መጻሕፍትን ጽፈዋል፤ አብዛኞቹ መጻሕፍት ኃይማኖታዊ ጭብጥ የያዙ ይሁን እንጂ ዓለማዊ ይዘት ያላቸውም ነበሩ፡፡ መጽሐፈ ብርሃን፣ መጽሐፈ ምዕላድ፣ እግዚአብሔር ነግሠ፣ ስብሐተ ፍቁር፣ መጽሐፈ ሥላሴ፣ መጽሐፈ ባሕርይ፣ ተዐቅቦ ምስጢር፣ ጦማረ ትስብእት፣ ድርሳነ መላእክት፣ ራእየ ተአምር፣ መልክአ ጉባኤ እና መንገደ ሰማይ በንጉሥ ዘርአ ያዕቆብ የተደረሱ መጻሕፍት ናቸው፡፡ በተጨማሪም በግጥም ቅርጽ የተሰደሩና በሥነ ግጥም አላባውያንና ማቅረቢያ ስልቶች ሊዳኙ የሚችሉ ቅኔዎችን አዘጋጅተዋል፡፡ እነዚህ ድርሳናት ያላቸው ይዘትና ሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳ በዚህ ስራ ተዳስሷል፡፡ ድርሰቶቹ የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍና ታሪክ ለመረዳትና ለማጥናት ፋይዳ አላቸው፡፡ በተጨማሪም ስራዎቹ ከሥነ ጽሑፍ ዋጋቸው ባለፈ

የኢትዮጵያን ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ታሪካዊ፣ ኃይማኖታዊና የፖለቲካ-ታሪክ ለማጥናት ጉልህ አገልግሎት አላቸው፡፡

ይህን ምርምር ለማድረግ አነሳሽ  የሆኑ ምክንያቶች አሉ፡፡ ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው በ15 ክ/ዘመን የዳበረ የትርጉምና ወጥ የሥነ ጽሑፍ ተግባር ነበረ፡፡ ሆኖም በሚገባው ልክ ትኩረት አግኝቶ አልተጠናም፡፡ በተለይ በዘመኑ የነገረ መጻሕፍትና የቤተ መጻሕፍት ጽንሰ ሃሳብ ጉዳይ በአያሌው የተቀነቀነ ነበር፡፡ የዐጼ ዘርዐ ያዕቆብ ሥነ ጽሑፎችም በአጥጋቢ ሁኔታ ተጠንተዋል ለማለት አያስደፍርም፡፡ መጽሐፈ ብርሃን ላይም ቢሆን በፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ ከተደረገው A New Text-Critical Introduction to Mashafa Berhan With a Translation of Book I፣ በጌታቸው ኃይሌ "The Homily of Zar'a Yaqob Mashafa Berhan"፤ እንዲሁም በሪቻርድ ፓንከርስት ከተሰራው የመጽሐፉ ትርጉም ውጪ ይህ ነው የሚባል ጥናት አልተደረገም፡፡ መጽሐፉን ወደ ሌሎች ቋንቋዎች በመመለሱ ረገድ ዲልማን (ወደ ጀርመንኛ)፣ ሪቺ (ወደ ጣሊያንኛ) ተርጉመዋል፡፡ የዐጼ ዘርዐ ያዕቆብ ድርሰቶች መጠናት እንዳለባቸው ይታመናል፤ እንዲሁም የ15ኛው ክ/ዘመን የእውቀት እንቅስቃሴ ምን ይመስል እንደነበር መጽሐፈ ብርሃንን በመመርኮዝ የዘመኑን ሁኔታ በይኖ የይሁንታ ሃሳቦችን ለመሰንዘር ይህ ጥናት ተደርጓል፡፡

የጥናቱ ዋና ዓላማ በዐጼ ዘርዐ ያዕቆብ የተደረሰው መጽሐፈ ብርሃን ምን አይነት ማኅበረ-ፓለቲካ፣ የፖለቲካ ታሪክ፣ የአገር ግንባታ፣ ባህላዊ የውዝግብ አፈታት ሃሳቦችን እንደያዘ ማሳየት ነው፡፡ በተጨማሪም የ15ኛው ክ/ዘመን የመጻሕፍትና የእውቀት ማዕከላት ሁነት ምን ይመስል እንደነበር ማሳየት፤ የመካከለኛውን በተለይ የ15ኛው ክ/ዘመንን የሥነ ጽሑፍ እንቅስቃሴ የመዳሰስ፣ የንጉሡን የሥነ ጽሑፍ ተሳትፎ በወፍበረር እግረ መንገዱን ማስቃኘት ንዑሳን ዓላማዎች ናቸው፡፡ ጥናቱ ስለመካከለኛው ዘመን ሥነ ጽሑፋዊ እንቅስቃሴ መረጃ ይሰጣል፡፡ በዘርፉ በተለይ በመካከኛው ዘመን ታሪክና ሥነ ጽሑፍ ላይ ግብዓት ይሰጣል፡፡ ለመካከለኛው ዘመን ጥናት፤ ማኅበረ-ፖለቲካ፣ ሃይማኖት፣ ታሪክ እና ስለእውቀት ማዕከላት ግንዛቤ በመፍጠር የቀጣይ ጥናት መነሻ ሆኖም ያገለግላል፡፡

የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ምንጮች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮች በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ በግእዝ ቋንቋ ተጽፎ በብራና ተሰንዶ የሚገኘው መጽሐፈ ብርሃን ነው፡፡ ሁለተኛ ደረጃ ምንጭነት ደግሞ በ15ኛው ክ/ዘመን የተጻፉ ድርሰቶች፤ እንደዜና መዋዕላት፣ ገድላት፣ ድርሳናት፣ በተጨማሪም ለጥናቱ የሚያግዙ መጻሕፍት እንደአካዴሚክ ጽሑፎችና ልዩ ልዩ ሰነዶች/መዛግብት እነሱም የጊዜውን ሁነት ለማሳየት የሚረዱ ብሎም ለተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት የሚሆኑ ልዩ ልዩ ጽፎች ናቸው፡፡ ጥናቱ በገላጭ (Descriptive) ወይም አይነታዊ (qualitative) ዘዴ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ መጽሐፈ ብርሃን በተጻፈበት ዘመን የተስተዋሉ ማኅበረ-ፖለቲካዊ አውዶች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

## 2. የአጼ ዘርዓ ያዕቆብ የሥነ ጽሑፍ ሕይወት

አጼ ዘርዐ ያዕቆብ ለዘመኑ ሥነ ጽሑፍ እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረው፡፡ ዘመኑ ትርጉምና ወጥ ጽሑፎች በብዛት የተጻፉበትና የተተረጎሙበት ዘመን ነበር፡፡ ንጉሡ በግሉ በርካታ መጻሕፍትን ደርሷል፡፡ የሥነ ጽሑፉ የበላይ ጠባቂ ወይም ተቆጣጣሪ ከመሆኑም በላይ ግለሰባዊ ቀጥተኛ ተሳትፎ ነበረው፡፡ በቤተ መንግሥቱ ጸሐፍትን አሰባስቦ ቀለብ ሰፍሮ፣ ለመጻፊያ ልዩ ስፍራ (scriptorium) አዘጋጅ መጻሕፍት እንዲደረሱ፣ እንዲተረጎሙ፣ እንዲባዙ በማድረግ ወደ ገዳማት እንዲሰራጩ ያደርግ ነበር፡፡ ሊቃውንት በጽሑፉ ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው እንዲጽፉ ልዩ ድጋፍና ማበረታቻ ያደርግ ነበር፡፡ በዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ሥነ ጽሑፍ አብቧል፡፡ ለዚህም የተለያዩ ሁነቶችን በምክንያትነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ እሱም፡- በዘመኑ ሰላም መስፈኑ (ከአውደ ውጊያ ድሎች ማግስት)፤ በሥነ ጽሑፍ ባዕድ አምልኮንና መተት-ጥንቆላን ለመዋጋት፤ የሃይማኖት ልዩነቶችና ምንፍቅና ምላሽ ለመስጠት እና ሥነ ጽሑፍን መሳርያ በማድረግ ክርስትናን ለማስፋፋት ናቸው፡፡

### 2.1. ሥነ ጽሑፍ በ"መካነ ብርሃን" ቤተ መንግስት

በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ቤተ መንግሥት (በመካነ ብርሃን) መካነ ጽሕፈት (Scriptorium) ለስሑፍ ስራ ተወስኖ የተዘጋጀ ስፍራ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ገዳማት እንደመካነ ጽሕፈት አገልግለዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ደብረ ሊባኖስ እና ሐይቅ እስጢፋኖስ (አባ ኢየሱስ ሞአ- ጽሕፈት ተምረው ወንጌልን ጽፈዋል)፤ በእነዚህ ገዳማት በተለይ ከልሳነ አረቢ ወደግእዝ የትርጉም ስራ ይከናወን ነበር፤ ቀደም ብሎ (በጥንታዊው ዘመን) ደብረ ዳሞ እና ግሸን የዚህን አይነት አገልግሎት ይከወንባቸው ነበር፡፡ ንጉሡ ሊቃውንቱን በደብረ ብርሃን ከተማ ሰብስቦ ነበር፡፡ ከእነዚህ ውስጥ እውቅ ጸሐፍቱ እነአባ ጊዮርጊስ፣ ቄስ ሐጼ ዘካርያስ እና የስጦስ ዘደብረ ማርያም ይገኙበታል፡፡ የጽሕፈት ማዕከል ሆኖ አገልግላል፣ በርካታ መጻሕፍት ተጽፈውበታል (አምሳሉ፣2011)፡፡ በቤተ መንግሥቱ መካነ ጽሕፈት አዘጋጅታል፤ መጻሕፍት ይተረጎማሉ፣ ይቀዳሉ፣ ወደምዕመናን፣ ገዳማት፣ አብያተ ክርስቲያናት ይሰራጫሉ፡፡ ለምሳሌ፡- "ድርሳነ ገብርኤል፣ መጽሐፈ ልደተ አበው፣ ገድለ የስጦስ፣ ጦማረ ትስብእት፣ ድርሳነ ሰንበት፣ ተዐቅቦ ምስጢርና መጽሐፈ ባህርይ" ተጠርዘው ከደብረ ብርሃን ወደ አበነ አብሳዲ ገዳም (ሰራዬ-ኤርትራ) ተልከዋል (አምሳሉ፣2011)።

### 2.2. አጼ ዘርዓ ያዕቆብ እና የድርሰት ስራ

በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ድርሰቶች ባለቤትነት ዙሪያ የሚነሱ ክርክሮች አሉ፡፡ ይህም መጽሐፍቱን እሱ አልደረሳቸውም የሚል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ንጉሡ ጀምሮ ሊቃውንቱ ጨረሷቸው የሚሉም አሉ፡፡ ነገር ግን ንጉሡ በራሱ እንጻፋቸው የሚያስረዱ ማሳያዎች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ገዳማት ላይ ከሊቃውንት ጋር ሰፊ ጊዜ ማሳለፉ ነው፡፡ ይሄም ለመንፈሳዊናፖለቲካዊ እውቀቱ መዳበር ሁነኛ ሚና እንደሚኖረው ይገመታል፡፡ በሌላ መልኩ በአጼ ዘርዐ ያዕቆብ ዜና መዋእል ላይ መጽሐፍቱን በሚደርስበት ወቅት በደብረ ብርሃን ከተማ ለ12 ዓመታት በተመሰጠ መቀመጡን ያወሳል፡፡ ዜና መዋዕሉ በዚህ ጊዜ ውስጥ፤ መጽሐፈ ብርሃን፣ መጽሐፈ ሚላድ፣ ጦማረ ትስብእት፣

ተዐቅቦ ምስጢር፣ ክህዶተ ሰይጣን እና መጽሐፈ ባህርይ የተሰኙ ድርሰቶቹን እንዳሰናዳ ይጠቅሳል፡፡ ሲኖዶስና ዲድስቅልያ የተሰኙ የቀኖና ድርሳናትም አጼ ዘርዐ ያዕቆብ የመጽሐፍ ደራሲ ለመሆኑ እማኝነት ይሰጣሉ፡፡ በሌላ በኩል መጽሐፈ ብርሃን የተሰኘው ድርሰቱም "…. *ዘመጽሐፈ ብርሃን ዘጸሐፈ ንጉሥነ ዘርዓ ያዕቆብ…" በማለት የመጽሐፉን ደራሲነት ለንጉሡ ይሰጣል፡፡* መጸሕፍቱ በአብዛኛው በዘመኑ ለተነሱ ሃይማኖታዊ ጥያቄዎችና ክርክሮች ምላሽ እንዲሆኑ ታስቦ ለሃይማኖቱ ካለው ቀናኤነት በመነጨ ለ"መልስ" የጻፋቸው ናቸው፡፡ ከወጥ ድርሰቶች በተጨማሪ መወድስ መዝሙሮች/ግጥሞች/hymns አሉት፡፡ ጽሑፎቹ መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆኑ ዓለማዊ ይዘት ያላቸውም እንደሆኑ ይታወቃል፡፡

## 3. መጽሐፈ ብርሃን የያዛቸው ሃሳቦች

መጽሐፈ ብርሃን ከአጼ ዘርዐ ያዕቆብ መጻሕፍት ውስጥ ዝነኛው ነው፡፡ መጽሐፉ የ15ኛው መቶ ክ/ዘመንን ኢትዮጵያ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኃይማኖታዊ መስተጋብር ይተርካል፡፡ በዘመኑ ለተሰሙ የሃይማኖት ተሃድሶ ጥያቄዎችና ክርክሮች ምላሽ ይሆኑ ዘንድ የተጠቀሱ ሃሳቦች አሉ፡፡ መጽሐፈ ብርሃን ስለኃላፊነትና ሹመት፣ ስለቀሳውስትና የካህናት አለቆች፣ ስለሥራ፣ ትዕዛዝና ይቅርታ፣ ስለትምህርት፣ የማስተማር ጥበብና ንባብ፣ ስለይቅርታና በሰንበት ስለመሰብሰን፣ ስለባዕድ አምልኮና ፍርድ፣ ከቦታ ቦታ ስለመዘዋወርና ስለቀኖና መጻሕፍት ያትታል፡፡

### 3.1. ሃይማኖታዊ ሃሳቦች፤

አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ሃይማኖትን ለሃገረ መንግስቱ ግንባታና መጽናት ተጠቅሞበታል፡፡ አንድቷ የጸና እና በወጥ ስርዓት የምትመራ ቤተ ክርስቲያን ሃገራዊ አንድነቱንና ዙፋኑን ለማጽናት እንደመሳርያ ተገልግሎበታል፡፡ በመጽሐፈ ብርሃን ንጉሡ በሃሳብና በስርዓት መልክ ያቀነቀናቸውን ሃይማታዊ አጀንዳዎች በዚህ ርዕስ ስር ተመልክተዋል፡፡

#### 3.1.1. ኃላፊነትና ሹመት

የጳጳሳት፣ የኤጲስ ቆጶሳት፣ የካህናትና የዲያቆናትን የኃላፊነትና የተግባቦት መስመርና የስልጣን ክፍፍልን በሰፊው ያትታል፡፡ በእነዚህ የስልጣን ክፍፍሎች የሚተገበሩ ኃይማኖታዊ ክዋኔዎችን ይዘረዝራል፡፡ ስለ ስርዓተ ቁርባን፣ ስለምስጢረ ጥምቀት፣ስርዓትና ሙሉ ሂደተ ክዋኔው ይናገራል፡፡ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ቀሳውስት (ካህናት) እና ሊቃነ ካህናት ከአሹዋሹዋም ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ወቅት መተግበር ስለሚገባቸው ኃላፊነትና የሥልጣን ተዋረድ ሁሉ ይዘረዝራል፡፡ ሐዋርያት በዲዲስቅልያ እንዳዘዙት የሃይማኖትን ቃል ለህዝብ ለማስተማር  ችላ እንዳይሉ ካህናትን ያስገዝባል፡፡ ካህናት በአንድነት እንደየስራ ድርሻቸው በትብብር ይሰሩ ያገለግሉ ዘንድም ያስገነዝባል፡፡

### 3.1.2. ስርዓተ እምነት እና ተያያዥ

ከሌላ እምነት አዲስ ለተመለሱ አማኞች መደረግ ስላለበት እንክብካቤ እና መከወን ስላለበት ስርዓት የሚያትትበት ክፍል አለው፡፡ ከነገረ ሃይማኖት ውስጥ አዲስ ወደክርስትና የተመለሱ አማኞችን በተመለከተ ስለሚደረግላቸው ክትትልና ስለሚፈጸምላቸው ስርዓት በተለያዩ ክፍሎች ላይ ያስረዳል፡፡ እንዲሁም ስለ የጥምቀት ስርዓት አፈጻጸም እና ክህነት ያላቸው ከጳጳሳት እስከ ዲያቆናት ባለ ደረጃ ያሉ የሃይመኖት አባቶች ስለሚፈጽሙት ስርዓት ከነስልጣን እና አገልግሎት ተዋረዳቸው የሚያትትበት ሰፋ ያለ ይዘት በመጽሐፉ ውስጥ አለ፡፡ በአብዛኛው ካህናትና ዲያቆናት ስላለባቸው መንፈሳዊ ኃላፊነት እያስገነዘበ የሚያብራራ ነው፡፡

ካህናት ትምህርተ ወንጌልን ማሰራጨት ዋነኛ ስራቸው እንደሆነ በአንክሮ ያስገነዝባል፡፡ እንደመጽሀፈ ብርሃን ካህናት አማኞችን ማስተማር ይኖርባቸዋል፡፡ ምዕመናንም በቀሳውስቱ የሚሰጠውን ትምህርት የመማር ግዴታ ይጣልባቸዋል፡፡ በካህናት ላይ የተላለፈው መልዕክት የእግዚአብሔርን ቃል በየቤቱ እሄዱ ማስተማር እንደሚገባቸው፤ ለመማር ፈቃደኛ ባልሆኑ ክርስቲያኖች ቤት እንዳይበሉ እንዳይጠጡም ያስገነዝባል፡፡

> ኢታጽርዑኬ ኦ ቀሳውስት ወዲያቆናት ዘልፈ ምሂረ ቃለ ሃይማት ለሕዝብ፡፡ ኀድጉሰ ለክሙ ወሕዝባውያንኒ ከመ ይትዋሥኡ በውስተ አብያቲሆሙ ዕደው ምስለ ዕደው ወአንስት ምስለ አንስት በቃለ ሃይማኖት ዘተምህሩ በቤተ ክርስቲያን አዘዘ እግዚእነ በመጽሐፈ ኪዳን (መጽሐፈ ብርሃን፤ 2010፡104)፡፡

ቀሳውስትና ዲያቆናት የሃይማትን ቃል ለህዝብ ማስተማርን ማቋረጥ እንደሌለባቸው ነው፡፡ ማስተማር ብቻም ሳይሆን ህዝቡም የተማሩትን ቃል በቤታቸው ውስጥ እንዲነጋገሩ ይመክራል፡፡ የክህነት ስልጣን ያላቸው እንደየ ስልጣናቸው ተዋረድ እርስ በርስ መታዘዝ እንዳለባቸው ያስገነዝባል፡፡

### 3.2. ተግባረ እድ፣ የቀለም ትምህርትና ጸሎት

እንደ ዘርዐ ያዕቆብ ሥራ ማለት በአፍ የሚነገርም በተግባር የሚከወንም ነው፡፡ ንጉሡ በስራ የሚያምን ነበር፡፡ ከሃይማኖት ምክንያቶች ባሻገር ወደጣኦት አምልኮና ጥንቆላ ቤት በሚሄዱ ሰዎች ላይ ሲያስተላልፍ የነበረው ከበድ ያለ ቅጣት ስራ መፍታትን ለማስወገድ ጭምርም ነው፡፡

> ስማዕኬ ለእመ ትትከሐድ እንዘ ትብል ነገርሰ ኢኮነ ግብር፡፡ ወግብርሰ ተግባረ እድ ውእቱ ኩሉ ዘይገብሮ እጓለ እመ ህያው በእዴሁ፡፡ ወንሕነኒ ንብለከ ቦኑ ግብረ እድ ለነገሥት ወለመኳንንት ወለአብልዕት፡፡ ወባሕቱ ቦሙ ነገረ ግብር ዘይትገበር በቃሎሙ ዘውእቱ ቃለ ፍትሕ ወትእዛዝ ዘኢኮነ ግብረ እድ፡፡ ወካዕበ ስማዕ ንንግርከ ፍካሬሁ በበጾታሁ፡፡ ፪ኤ ጾታ ግብር፡ ፩ ጾታ ነገረ ግብር ውእቱ፡ እመሂ ለእከይ ወእመሂ ለሠናይ፡፡ ወካልኡ ጾታ ግብር ተግባረ እድ ውእቱ፡ ኩሉ ሰብእ እድ ወአንስት ዘይገብር ግብረ እድ፡፡ ብእሲ ዘይገብሮ

> በእዴሁ እመሂ በተገብሮ ገራኅት ወእመሂ በፍኖት ዘንተ ወዘይመስሎ ዘኮነ ከዊኖ ወኩሉ ግብረ እጓለ እመህያው (መጽሐፈ ብርሃን 2010፡88)፡፡

በመሆኑም ስራ በአፍም በእጅም ሊከወን ይችላል፡፡ የነገር ስራ ወይም በአፍ ቃል በማውጣት ከሚሰሩት ውስጥ ነገሥታትን፣ አስተዳዳሪዎችንና ባለጠጎችን ያስቀምጣቸዋል፡፡ አንደኛው ስራ የቃል ሲሆን እሱም የበጎነት አሊያም የክፋት ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላኛው ደግሞ ማንኛውም ሰው በእርሻ ቦታም ይሁን በመንገድ ሲጓዝ ሊሰራው የሚችል የእጅ ሥራ እንደሆነ ይናገራል፡፡

በሌላ ወገን፤ ሴት ልጅ ስለምትሰራቸው ስራዎችም ልዩ ልዩ የእጅ ስራዎች ሰሎሞንን በመጥቀስ በሰፊው ያትታል፡፡ ሰሎሞን ሴት በምን አኳኋን ሰርቷ ቤቷን እንደምታቆም፣ ባሏንም እንደምትረዳ ያሰፈረውን በመጥቀስ ስለሴት ልጅና ስራዋ ሃተታ አስፍሯል፡፡ *"ወብእሲትኒ ጽንዕት ወኀሪት ትገብር በእደዊሃ ከመ ትርድኦ ለምታ በከመ ይቤ ሰሎሞን ትትራድኦ ለምታ ሰናየ በሠናይ ወዘእኩይ በኩሉ ሕይወታ እንተ ትቤዝት ጸምረ"* (መጽሐፈ ብርሃን 2010፡88)፡፡

ጥበበኛ ሴት ከእጅ በተጨማሪ የቃል ስራም እንዳላት ያስረዳል ይህም አፏን በሕግ እንደምትከፍትና ለምላሷ ወሰንን እንደምትሰራ ነው፡፡ እንደዘርዐ ያዕቆብ አፍን በሕግ መክፈት ማለት ለአንደበት ወሰንን መስራት ማለት ነው፡፡ በማለዳ አፍን መክፈት ቅድሚያ ለጸሎት መሆን እንዳለበት ያስረዳል፡፡ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች ለመጸለይ ካልሆነ በቀር ለምንም አይነት ሥጋዊ ስራ በማለዳ ቀድመው አፋቸውን እንዳይከፍቱ ያዛል፡፡

አዳም ከገነት በወጣ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት እጣን ማጨሱን ይህም የስራ አጀማመር እንደሆነ ያወሳል፡፡ የእስራኤል ልጆችም የቤተ መቅደስ ማሰሪያ የሚሆን ስጦታ መሰብሰባቸውን በዚሁ አውድ ያነሳል፡፡ ሴቶችም ወንዶችም የማለዳ ስራቸውን (ጸሎት) ጨርሰው እንደተመለሱ ወደሥራቸው (የገቢር ክንዋኔ) እንዲሰማሩ ያዛል፡፡ ጸሎት እንደዋነኛ ሥራ ሆኖ ነው የቀረበው፡፡ ከጸሎትም በተጨማሪ የሃይማትን ቃል ለመስማት ወደ ትምህርት ቤት መሄድ ግድ ነበር፡፡ ወደ ሥጋዊ ሥራ መሄድ የሚበረታታውም ከጸሎትና ከትምህርት በኋላ ነው፡፡

### 3.3. መጻሕፍት፣ ንባብ እና በትምህርት መጽናት፤

ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ ለመጻሕፍት ልዩ ፍቅር ነበረው፡፡ የሃገረ መንግስቱን ግንባታና የአንድነት መሰረት በመጻሕፍት በሰፈሩ እውቀት ሊያጸና ሞክሯል፡፡ ለመጻሕፍት ካለው ፍቅር የተነሳ ንጉሡ ራሱ በእጁ ከሚደርሳቸው መጻሕፍት በተጨማሪ ለህዝብ እና ለመንግስቱ መጽናት ይጠቅማል ያላቸውን መጻሕፍት ከውጭ አገራት ቋንቋዎች ላይ ወደግእዝ በሊቃውንቱ አማካኝነት ያስተረጉም ነበር፡፡ ካስተረጎማቸው መካልም ዜና አይሁድ፣ ፍትሃ ነገሥት፣ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ፣ አቡሻኽር፣ ስንክሳር እና ተአምረ ማርያም ይገኙበታል፡፡

> ወለመጻሕፍትሰ ብዙኅ አናቅጽ ቦን፡፡ ወለእመ ቦ ዘቦአ ውስተ ኩሎን አናቅጽ ሠናየ ምርዓየ ይረክብ፡፡ ወእመሰ ቦአ ውስተ አሐቲ አንቀጽ፡ ወለእመኒ ይቤ ዛቲ አሐቲ አንቀጽ ትበቁዓኒ ፍጡነ ይትዓቀፍ ወይወድቅ፡፡ ባኡኬ በአእምሮ ውስተ ብዙኅ አናቅጺሆን ለመጻሕፍት ዘጽድቅ እለ ይትበደራ እምወርቅ

*ወእምጻዝዮን ዕንቁ እንዘ ትስዕልዎ ለእግዚአብሔር ከመ ትተዓቀቡ እምተዓቅቦ ወእምወዲቅ* (መጽሐፈ ብርሃን፤ 2010፡96)፡፡

በዚህ ጥቅስ ውስጥ በግልጽ የሚታየው ንጉሡ ስለመጻሕፍት ያለውን ቀናኢነትና በእውቀት የማመኑን ነገር ነው፡፡ እንደዘርዐ ያዕቆብ መጻሕፍት ብዙ በሮች አሏቸው፡፡ በእነዚህ በሮች የሚገባ መልካም ሕይወትን ያገኛል፡፡ ከእውቀት ዛፍ ፍሬም ይመገባል፡፡ እውቀት በመጠን የተወሰነ አለመሆኑን፤ ከእውቀት (ከመጻሕፍት) ብዙ በሮች ውስጥ በአንደኛዋ ብቻ ብገባ ይበቃኛል የሚል ቢኖር ቁንጽል እውቀት እንደሚያጠፋ እያስገነዘበ፤ በሁሉም የመጻሕፍት በሮች ግቡ በማለት የተጻፈ ሁሉ ተነቦ ሊመረመር እውቀትም በጥልቀት ሊያዝ እንደሚገባ ያስረዳል፡፡ እናም መጻሕፍት ከወርቅ፣ ከአልማዝና ከዕንቁ የሚመረጡ ሰዎች በማስተዋል ገንዘብ ሊያደርጓቸው እንደሚገባም ይናገራል፡፡

ለመጻሕፍትና ለንባብ ካለው ጉጉት የተነሳ ንጉሡ ራሱ ከመጻፍ፣ ከማጻፍና ከማስተርጎም በተጨማሪ ሊቃውንትን በቤተ መንግሥቱ ቅጽር ውስጥ ደመወዝ በመቁረጥ ሙሉ ጊዜያቸውን ለመጻፍና ለመመርመር እንዲሁም ለመተርጎም እንዲያውሉ ያደርግ ነበር፡፡ ስርዓተ ፍትሃትነቱ እንዳ ሆኖ ለመጻሕፍት ካለው ፍቅር በመነሳትም ይመስላል ለሙታን እንኳ ከሚደረጉ ስርዓቶች ውስጥ አንዱ መጻሕፍትን በሙታን ላይ ማንበብ አስፈላጊ ስለመሆኑ በአጽንኦት ያስቀምጣል፡፡ *"…ወአንብቡ መጻሕፍተ ቅዱሳተ ላዕለ እለ አዕረፉ ክርስቲያን ጻድቃን ወሰማዕት አኃዊክሙ እለ አዕረፉ በአሚነ ክርስቶስ"* (መጽሐፈ ብርሃን፤ 2010፡110)፡፡

ትምህርትን በትምህርት ቤቶች ጸንቶ በመቆየት መማር እንደሚገና ይናገራል፡፡ *"…ሰምዑ ንንግርክሙ ኩልክሙ ማኅበረ ቤተ ክርስቲያን ዘየዐቢ እምኩሉ ምግባረ ሠናይ ወጽድቅ አጽንዖ መካነ ትምህርት ወተጋብኦ በሰንበት ወበእሑድ ለሰሚዓ መጻሕፍት ቅዱሳት ዘመለኮት እምኩሉ ትእዛዝ"* (መጽሐፈ ብርሃን፤ 2010፡134)፡፡ መጽሐፈ ብርሃን ከተጻፈበትና ለህዝብ ከተሰራጨበት ዓላማዎች ውስጥ አንዱ ይህ በትምህርት በዓት ወይም ገበታ ስለመጽናት መጻሕፍትን ስለመስማትና መመርመር ነው፡፡ በትምህርት ቤት ከመጽናት በተጨማሪ በሰንበታት ማለትም በቅዳሜና እሁድ ቀናት ሕዝብ በቤተ ክርስቲያን ተሰብስቦ ከሁሉም የሚበልጠውን የመጻሕፍትን ነገር መስማት እንዳለበት ይመክራል፡፡ እንሚታወቀው በዘመነ ዘርዓ ያዕቆብ የአያሌ ስርዓቶች ድንጋጌ ተጀምሯል፡፡ ከእነዚህ አዳዲስ ስርዓቶች ውስጥ አንዱ በሰንበት በቤተ ክርስቲን ተሰብስቦ መጻሕፍትን ሲነበቡ መስማት ነው፡፡ ለምሳሌ አሁን ድረስ ተአምረ ማርም ህዝብ በተሰበሰበበት እሁድ ጠዋት በሁሉም ቤተ ክርስቲያናት ይነበባል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም ሰዎች የመጻሕፍትን ቃል ይሰሙ ዘንድ ነው፡፡ አንድም ትምህርትን ሁሉም ላይማር ይችላልና ላልተማሩቱ በጆሯቸው ይሰሙ ዘንድ ሲሆን፤ አንድም መጻሕፍቱ በእጅ የሚገለበጡ እንደመሆናቸው በብዙ ቅጂ ማዳረስ ስለማይቻል በብዛት በመሰብሰብ በጆሮ ይሰሙታል፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍትን የሚያነቡና የሚያስተምሩ የነፍስን ሞት እንደማይሞቱ ተጽፏል፡፡ ይህም ለንባብና መጻሕፍት ምን ያክል ትኩረት እንደተሰጠ ያሳያል፡፡ ዮሐንስ አፈወርቅ *መጥፎ ሐሳብ*

*ወደአንተ ቢመጣ፣ ሠይፍህን ምዘዝ፤ እነዚህም የእግዚአብሔር መጻሕፍት ናቸው፡፡* ያለውን ጥቅስ ይጠቅሳል፡፡

> *ወዮሐንስ አፈወርቅ ይቤ እስመ ኀይሎሙ ለመጻሕፍተ እግዚአብሔር ያርኅቁ ጌጋየ እምልብ፡ ወይትወሃቦ አእምሮ ለዘያነብብ አስተርክቦ ወአእምሩ ከመ አነ ውእቱ እግዚአብሔር፡፡ ወበነቢይነ ይቤ እግዚአብሔር ይነግሮሙ ለሕዝቡ በመጽሐፍ፡፡ ወሰሎሞንኒ ይቤ እስመ አእምሮትከ ፍጽምት ጽድቅ ይእቲ፡፡ ወአእምሮተ ጽንዕከ ሥርወ ኢመዊት ይእቲ* (መጽሐፈ ብርሃን፤ 2010፡136)፡፡

መጻሕፍት በደልን ከልብ እንደሚያርቁ ይናገራል፡፡ ቅዱሳት መጻህፍትን የሚያነብና የሚያስተምር ከእግዚአብሄር ዘንድ እውቀትን እንደሚያገኝ ጽፏል፡፡ ሰዎችም የእግዚአብሔርን መጻሕፍት መስማትን እንዲዉ ይጠይቃል፡፡ ሁልጊዜ መጻሕፍትን ማንበብም እንደሚገባም ተጠቁሟል፤ ወደ በጎ ነገር እንደሚያደርስ ተገልጹዋል፡፡ ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ የሰነፈ ወይም ያቋረጠ ግን ታላቅ ጥፋት ይሆንበታል፡፡

ትምህርትን ስለማስቀደም በተናገረበት አንቀጽም ካህናት የሃይማኖትን ቃል ለህዝቡ ሳይታክቱ ማስተማር እንዳለባቸው ይመክራል፡፡

> *ወካዕበ አጽምኡነ በዕዝነ መንፈስ ኦ ካህናተ ወንጌል ቀሳውስት ወዲያቆናት መሀርዎሙ ዘልፈ ቃለ ሃይማኖት ለሕዝብ ለዕድ ወለአንስት እመሂ በፍኖት ወእመሂ በቤት ወበኩሉ መካን ኀበ በጻሕክሙ፡፡ ወመሀርዎሙኬ ለሕዝብ ወገስጽዎሙ ወትረ ዘእንበለ ሀኬት ለእመ ኢከልአክሙ ኀዘን ወሕማም፡ ወኢይደልዎክሙ ትብልዑ ወትስተዩ መብልዓ ሥጋዌ ወስቴ ሥጋዌ፡ እምቅድመ ትብልዑ ወታብልዖሙ፡ እምቅድመ ትስተዩ ወታስትይዎሙ ከመ ኢትሙት ነፍሶሙ በረሀብ ወበጽምዕ፡፡ መብልእሰ ወስቴ ቃለ አሪት ወነቢያት ወቃለ ወንጌል ወሐዋርያት* (መጽሐፈ ብርሃን 2010፡86)፡፡

በዚህ ቅንጭብ መሰረት ካህናት የሃይማኖትን ቃል ለህዝቡ በመንገድም ይሁን በቤት ውስጥ ወይም በደረሱበት ቦታ ሁሉ ዘወትር ያለመታከት ማስተማር እንዳለባቸው ያሳስባል፡፡

**የማስተማር ጥበብን በተለመከተ፤** አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል መማርን ቸላ እንዳይሉ ካህናቱም ለማስተማር እንዳይሰንፉ ያሳስባል፡፡ በማያምኑ ሰዎች አካበቢ በሚሄዱ ጊዜ ባህላቸውን እና ወጋቸውን በመምሰል ቀርቦ ወደክርስትና መመለስ እና የሥላሴ ልጅነትን ሊሰጧቸው እንደሚገባ ያስተምራል፡፡ ጳውሎስን በማያኑ ሰዎች ሃገር ሄዶ የተከተለውን ጥበብ እንደማሳያ በማድረግ ካህናት ሊከተሉት ስለሚገባ የማስተማር ጥበብ ያስረዳል፡፡

ካህናት ጥበብ በተሞላበት መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር እንዳለባቸው ሲያስገነዝብ ከቀደምት በመጽሐፍ ቅዱስ ከተጠቀሱ የሃይማኖት መምህራን ማለትም ዕዝራን፣ ዮሐንስ መጥምቁ፣ ኤልያስ፣ ዔሊ፣ ሐዋርያት፣ ዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ፣ ዳዊት፣ ጳውሎስን እየጠቀሰ ምክር ይሰጣል፡፡

ንጉሡ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ንባብን እና ድርሰትን የሚያበረታታ ንጉሥ ነው፡፡ ጽሑፍና መጻሕፍትን ከማበረታታት በዘለለ ደራሲም ሲሆን ከ10 በላይ መጻሕፍትን ጽፏል፡፡ መጽሐፈ ብርሃን፣ መጽሐፈ ሚላድ፣ እግዚአብሔር ነግሠ፣ ጦማረ ትስብእት፣ ራዕየ ተአምር፣ ስብሃተ ፍቁር እና ከሂዶተ ሰይጣን ከድርሰቶቹ ውስጥ ይጠቀሳሉ፡፡ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ሌሎች መጻሕፍትንም እንደደረሰ ይታመናል፡፡ መልክአ ጉባኤ እና መንገደ ሰማይ የተሰኙ የንጉሡ መጻሕፍት በፓሪስ መታተማቸውን አክሊለ ብርሃን ጠቅሰዋል፡፡ (አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ፤ 1945)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ልዩ ልዩ የውዳሴ መዝሙሮችም /Hymns/ አሏቸው፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት መጻሕፍት ውስጥ "ስብሃተ ፍቁር" እና "እግዚአብሔር ነግሠ" በግጥም መልክ የቀረቡ ስራዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪ በተለያዩ አጋጣሚዎች የተቀኛቸው ቅኔዎች (ለምሳሌ፡- ለአባቱ ክብር መታሰቢያ በሞቱ ጊዜ የተቀኘው አለ) እና መወድሶች አሉ፡፡ የአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ከሚታወቅባቸው ሁነቶች አንዱ የውጪ ግንኙነት ነው፡፡ ደብዳቤዎች ከተለያዩ ዓለም አገራት መንግስታት ጋር ይለዋወጥ ነበር፡፡ በዚህ ረገድ ጉባኤ ፍሎረንስንና ሚስቱ ንግሥት ኢሌኒ የነበራት ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ችሎታ ብሎም የውጪ ግንኙነት ጥበብ የሚጠቀስ ነው፡፡ በሃይማኖት ውዝግብ ወቅትም ማስገንዘቢያ ጦማሮች ይጻፉ ነበር፡፡ እነዚህ ሁሉ ለሥነ ጽሑፉ እድገት ወሳኝ ሚና ነበራቸው፡፡

### 3.4. ሙታን እና ይቅርታ፤

ለሞቱ ሰዎች ስለሚደረግ ስርዓት የሚናርበት ክፍል አለ፡፡ ክርስቲያኖች በሞቱ ጊዜ፤ ለክርስቲያን ክብር ስለሚገባ፤ ዲያቆኑ አስክሬናቸውን የማስጌጥና የመገነዝ ስርዓት ይከውናል፡፡ *"ወከመዝ ሥርጋዌሆሙ ለክርስቲያን ታሠረግዎሙ በስብሐት ወዘምሮ ማኅሌት ወበመዓዛ ዕጣን በጸሎት ወበአንብቦ መጻሕፍት ዘመለኮት ወበአዕርጎ ቁርባን"* (መጽሐፈ ብርሃን፤ 2010፡108)፡፡ በማለት ከግንዘት በኋላ እስከ ግብአተ መሬቱ ድረስ በምስጋና፣ በዝማሬ፣ በጸሎት፣ በእጣን መዓዛ፣ መለኮታዊ መጻሕፍትን በማንበብና ቁርባንን በማሳረግአክብሮ መሸኘት እንደሚገባ ያትታል፡፡ ካህናት ሞተው በሚገነዙበት ጊዜ ግን  በሥጋቸው ላይ ከርቤ በመጨመር ይገነዙ ዘንድ ያዛል፡፡ ስለሞቱት መዘመር፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ፣ መጸለይና በስማቸው ምጽዋት መስጠት የተገባ ሆኖ ቀርቧል፡፡

*"ወእለ አምኑ በእግዚአብሔር እመኒ ኖሙ ኢኮኑ ምውታነ፡፡ ጥቀ ሐዋዝ ሥርጋዌሆሙ ጸሎት ወስብሐት በመዝሙር በምጽዋት ወአንብቦ መጻሕፍት ቅዱሳት ወአዕርጎ ቁርባነ ሥጋሁ ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ለእለ አዕረፉ ማኅበረ ቤተ ክርስቲያን በአሚነ ክርስቶስ"* (መጽሐፈ ብርሃን፤ 2010፡110)፡፡ እንዳለው በእግዚአብሔር የሚያምኑ ቢሞቱ እንኳ አንቀላፉ እንጂ የሞቱ አይደሉም፡፡ ክብራቸው በመዝሙር፣ በጸሎት፣ በምስጋናና በምጽዋት የሚገለጽ በመሆኑ፡፡

ይቅርታ በዚህ መጽፍ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው፡፡

> ወእግዚእነሂ ይቤ በመጽሐፈ ኪዳን ወለእመቦ ዘተኀየሰ ምስለ ቢጹ ይኅድግ ሎቱ፡፡ ወኢያንብር ቂመ ወጽልዓ ወቅንዓተ ሳዕለ ቢጹ፡፡ ወእንዘ ከመዝ ሥሩዕ

ወእቱ አቁርሮ መዓት ዘእንበለ ይዕርብ ፀሐይ፡ ወከመ ይኅድግ ሎቱ ቢጽ ለቢጹ ለዘተኀየሰ ምስሌሁ (መጽሐፈ ብርሃን፤ 2010፡96)፡፡

ይቅር መባባል ለተጣሉ ሁሉ የሚገባ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ በጓደኛ ላይ ቂም መያዝ፣ ጥላቻና ቅናት መቋጠር መልካም እንዳልሆነ ደንግጓል፡፡ የበደለም “ይቅር በለኝ” ብሎ እንዲጠይቅ ሲያዝ፤ ተበዳይም ይቅርታውን እንዲቀበለው ግድ ይላል፡፡ ጉዳዩም በማግስቱ ወይም በሶስተኛው ቀን በፍቅር ያለ ጥላቻ በካህናት ሽምግልና እንዲቋጭ ያዛል፡፡

### 3.5. አምልኮ ባዕድ፤

ባዕድ አምልኮ በ15ኛው ክ/ዘመን በሰፊው ናኝቶ የነበረ ክስተት ነው፡፡ ህዝቡ በስፋት የሚያመልካቸው ታዋቂ ጣዖታትም ነበሩ፡፡ እንደ ደስክ፣ ዲኖ፣ ጉዳሌ፣ ፈጸንትና ጸግዊ የተባሉ ጣዖቶች ዘርዓ ያዕቆብ ነግሶ በነበረበት ጊዜ ነበሩ፡፡ በመሆኑም ንጉሡ ካህናቱ እንዲያስተምሩ ከማድረግና በመጻሕፍት ጉዳዩን ከማስገንዘብ አቅም በላይ ሲሆንበት ከፍተኛ ቅጣትን የገዛ ቤተሰቡን ሳይቀር እንዲቀጣ አስገድዶታል፡፡

በዚህ በመጽሐፈ ብርሃን መጽሐፍ አምልኮተ ባዕድ ከዋነኛ ይዘቶች ውስጥ ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱትና ሌሎችንም ጣዖታት የሚያመልክ ወይም ኮከብ ወደሚቆጥሩ፣ ወደ መሰሪዎች፣ ጠንቋዮችና አስማተኞች የሚሄድ ንስሃ ሳይገባ ወደ ትምህርት ወደሚሰጥበት ቦታ ወይም ቤተ ክርስቲያን መግባት እንደማይችል ጣዖትን ማምለክ ከኃጢአቶች ሁሉ የከፋ መሆኑን በመግለጽ ያስገነዝባል፡፡

በ1421 ዓ.ም አጼ ይስሐቅ ካረፈ በኋላ የስልጣን ሽኩቻና ግድያ በቤተ መንግስቱ ሲካሄድ ከቆዩ በኋላ አምባ ግሸን በግዞት ካለበት መጥቶ በ1426 ዓ.ም ዘርዓ ያዕቆብ እንዲነግሥ ሆነ፡፡ የንግሥና ዘመኑ ግን የረጋ አልነበረም፡፡ ጦርነቶች ከየአቅጣጫው ተከፍተዋ፤ የቆዩ የሃይማኖት ውዝግቦች እንደአዲ አገርሽተዋል፡፡ እንደጌታቸው ኃይሌ (2010፡37) ቅዳሜን እንደእሁድ ትከበር የሚሉ የአባ ኤዎስጣቴዎስ (ተከታዮቻቸው ኤዎስጣቴዎሳውያን)፤ ለሰውና ለመላዕክት፣ ለስዕል (ለማርያም) እና ለመስቀል አንሰግድም (እጅ አንነሳም) የሚሉ አባ እስጢፋኖስ (ተከታዮቻቸው እስጢፋኖሳውያን/ደቂቀ እስጢፋ[ኖስ])[2]፤ አምላክ መንፈስ እንጂ እንደፍጡር መልክ የለውም የሚሉ አባ ዘሚካኤል (ተከታዮቻቸው ዘሚካኤላውያን) ተነስተው ነበር፡፡ የዚህ መጽሐፍ አብዛኛው ክፍልም የሃይማኖት ስርዓት ላይና ጸረ-አምልኮተ ባዕድ ሃተታዎች ላይ በብዛት ያተኮረው ለእነዚህ የሃይማት ክርክሮች አንድም ምላሽ፣ አንድም ማስጠንቀቂያ ንጉሣዊ ቃል ይሆን ዘንድ ነው፡፡

ይሄን ሃሳብ ጌታቸው ኃይሌ ያጠናክሩታል፡፡

[2] ይህ አስተምህሮ ቀደም ብሎ በአጼ ያግብአ ጽዮን (1278-1286 ዓ.ም) የነበረ ጭቅጭቅ ሲሆን እንደገና አንስተውት ነው፡፡ (ጌታቸው 2010)፡፡

> ዘርአ ያዕቆብ መጽሐፍ ዐዋቂና ለሃይማኖቱ (ለእምነቱ) ቀናተኛ ከመሆኑ በላይ እነዚህ ሰዎች ህዝቡን (በተለየም መንግሥቱን) የሚከፋፍሉበት መስሎት ትልቅ ስጋት አደረበት፤ ጥያቄያቸውን መመለስ የራሱ ጉዳይ አደረገው፡፡ እስጢፋኖሳውያን ተከሰው ከንጉሡ ችሎት ሲቀርቡ እጅ መንሣትን እንደስግደት ቆጥረው ዝም ብለው ከፊቲ ሲቆሙ ጊዜ የባሰውን ይናደድ ነበረ፡፡ ... ዘርአ ያዕቆብና ደብተራዎቹ ለዘመኑ ችግር መፍትሔ ለመስጠት ብዙ ድርሳናት ደርሰዋል (ጌታቸው ኃይሌ፣ 2010፡37-38)፡፡

ንጉሡ ባለው የመንግስቱ ስልጣን ኃይል ተጠቅሞ ብቻ ጣኦት አምላኪዎቹ ላይ ቅጣት አላደረገም፡፡ የሚከተለውን ጥቅስ እንይ፡- *“ንዑኬ ተመየጡ ኀበ ንስሐ አ መምለክያነ ጣዖት ወእለ ትሴአሉ ጠንቋልነ ወትትኤመሩ በሐሳበ ከዋክብት፡፡ ወአምልክዎ ለእግዚአብሔር በንጹሕ ልብ ወኢትኀፈሩ ነገረ ጌጋይክሙ በኩሉ ጊዜ እስመ የኃድግ እግዚአብሔር አበሳክሙ”* (መጽሐፈ ብርሃን፤2010፡142)፡፡

ሃይማኖትንና ስርዓትን ለመጠበቅ እንደንጉሥ በኃይል እርምጃ እንደሚወስድ ሁሉ፤ እንደሃይማኖት ሰውም መጽሐፍ እየጠቀሰ፣ስርዓትን እያወሳ ወደቤተ ጣኦት የሄደ ሰው ይመለስ ዘንድ ይማጸናል፡፡ ከላይ በተጠቀሰው ቅንጭብ የምንረዳው ንጉሡ ጠንቋዮችንና ኮከብ ቆጣሪዎችን የሚማጸኑ ሰዎችን ከድርጊታቸው እንዲመለሱ ሲጠይቅ፤ የሚጸጸቱ ከሆነ እግዚአብሔር ይቅር እንደሚላቸው ሲያስገነዝብ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ንጉሡ በሰፊው ስሙ ተነስቶ የሚተችበት የደቂቀ እስጢፋኖስና እንዲሁም የቅዳሜ ሰንበትነትና የዘሚካኤላውያንን ጉዳይ በውይይት ለመፍታት ብዙ ርቀት እንደተጓዘ ይታወቃል፡፡ እስጢፋኖሳውያን ከሊቃውንት ጋር እና ከራሱ ከንጉሡ ጋር ጉባኤ ተዘርግቶ ተወያይተዋል፣ ተሟግተዋል፣ ተከራክረዋል፡፡ ዛሬ ግዘፍ ነስቶ የሚስተጋባው የንጉሡ ቅጣት የመጣው ከዚህ ተከትሎ ነው፡፡

በዚህ መጽሐፍ ንጉሡ የኢትዮጵያ ሰዎች ሃይማኖት ከሌሎች የበለጠ ደገኛ እንደሆነች ይናገራል፡፡ ኢትዮጵያውያኑም በብዙ ሃገራት ከሚኖሩ ሰዎች የበለጠ ደጋግና የሃይማትን ትምህርት የሚወዱ እንደሆነ ይናገራል፡፡ የኢትዮጵያ ሰዎች ሃይማኖት እንደፀሐይ የምታበራ እንደሆነች፤ ፀሐይ ከጨረቃ የበለጠች እንደሆነችው፣ ወርቅም ከብር እንደሚልቅ፤ የኢትዮጵያውያን ሃይማትም ከሌሎች ክርስቲያኖች ሃይማኖት የበለጠ የከበረች መሆኑን ይናገራል፡፡ በጥንት ጊዜ ሆሜር እና ሄሮዱቶስ የተባሉ የግሪክ የታሪክና የሥነ ጽሑፍ ሰዎች ስለኢትዮጵያውያን ደግነት፣ መልክ፣ ቁመና እና ጸባይ መጻፋቸው ይታወቃል፡፡ ይሄን ሁሉ ተላልፎ በጣኦት አምልኮ የተገኘ ሰው ቅጣቱ ከባድ ነበር (ታደሰ 1972፡235)፡፡

### 3.6. ነገረ-መጻሕፍት እና የመጻሕፍት ቁጥር

ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ የመጻሕፍት ሊቅ ነው፡፡ በ*መጽሐፈ ብርሃን* ላይ ስለቅዳሜና እሑድ አከባበር እንዲሁም ይህንን ለመማር በመንፈሳዊ ትምህርት ቤት ስለሚደረግ ጉባኤ ሕግ ሲደነግግ ብቻውን እንዳላደረገው ይልቁንም የጳጳሳቱ አባ ሚካኤልና አባ ገብርኤል ይሁንታ እንደታከለበት ይናገራል፡

: በዚሁ የመጽሐፉ ክፍል (ቀዳሜ ቃል ዘጸጳሳት ዘተደገመ) ጸጳሳቱ ንጉሡ የመጻሕፍት ሊቅ እንደሆነ ይመሰክራሉ።

ንጉሡ ስለመጻሕፍት ጥልቅ እውቀት ያለው መሆኑን *መጽሐፈ ብርሃን* ያነበበ ሰው ይገነዘበዋል። በመጽሐፉ ውስጥ ከብሉይ፣ ከሃዲስ፣ ከሊቃውንትና ከስርዓት መጻሕፍት የተውጣጡ የመጻሕፍት ዝርዝሮችን ከ200 ጊዜ በላይ ጠቅሷል። የመጻሕፍት እውቀቱንና መጽሐፉን በበቂ አጣቅሶ በእውቀትና በመረጃ አስደግፎ እንደጻፈው መረዳት ይቻላል።

ከንባብ ጋር ተያይዞ፤ በሰንበት ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው እንዲማሩ ካህናቱም ይሄን ተግተው እንዲፈጽሙ አዟል፡ በአቅራቢያ ቤተ ክርስቲያን ሌለባቸው አካባቢዎች ሰዎችን ደግሞ መጽሐፍ አዋቂ የሆኑ ካህናት በኃላፊነት እንዲያስተምሯቸው ያዛል። ቅዳሜና እሑድ በሰንበትነታቸው ከመከበራቸው ሌላ የመጽሐፍ መማሪያ (ማንበቢያ-በመስማት) ጊዜያት ናቸው።

ወደትምህርት ቤት ለመምጣት ፈቃደኛ ያልሆነ ሰው በአገሩ ሹም እንዲገረፍ፣ ይህን ትምህርት ቤት አልሄድ ያለውን ሰው ለመግረፍ ፈቃደኛ ያልሆነ ሹም ደግሞ በንጉሡ ትዕዛዝ ሃምሳ ጊዜ በአለንጋ እንዲገረፍ፣ ሶስት መቶ ጊዜ እንዲሰግድ፣ በደረቅ እንጀራና በውሃ ብቻ ለአንድ ሰምንት እንዲጾም ህግ ሰርቷል (ገጽ 182)። ሹመት የተሰጣቸው ካህናትም ተግተው የማያስተምሩ ከሆነ በማስተማር ለሚልቋቸው ሰዎች ሹመታቸው ተላልፎ እንዲሰጥ ወስኗል (183)። የመጻሕፍት ቁጥርን በተመለከተ፤ የቀኖና መጻሕፍት ማለትም፣ መጽሐፈ ሲኖዶስ፣ መጽሐፈ ዲዲስቅልያና መጽሐፈ ኪዳን ከ81ዱ መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ መካተት እንዳለባቸው በጽኑ ያስረዳል (ገጽ 203)። ከ81ዱ ጋር አይደመሩም ብለው የሚቃረኑትንም ይቃወማል። ማስረጃ እየነቀሰ ያስረዳል፡ : መጽሐፈ ሄኖክም እንዲሁ ተራው ከቅዱሳት መጻህፍት እንደሆነ ሐዋርያትንና ነቢያትን በእማኝነት እየጠቀሰ ያስረዳል (ገጽ 213)።

## 4. መደምደሚያ

ጥናቱ ትኩረቱን በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ የተደረሰው *መጽሐፈ ብርሃን* ላይ ያደረገ ነው። ዘመኑ የግእዝ ሥነ ጽሑፍ በጣም አብቦ የነበረበት ሲሆን በርካታ መጻሕፍት የተጻፉበትና የተተረጎሙበት ዘመን ነው። መካከለኛው ዘመን በኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ጉልህ ቦታ አለው። የመካከለኛው ዘመን የሥነ ጽሑፍ ውጤቶች ለኢትዮጵያ ታሪክና ሥነ ጽሑፍ ጥናት ምንጭነታቸው የጎላ ነው። ፋይዳቸው የኢትዮጵያን የፖለቲካና ሥነ መለኮታዊ ታሪክ ከመመረመርና ከማወቅ ይሻገራል። ስራዎቹ የዘመኑን ኅብረተሰብ ማኅበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ለመገንዘብና ለማጥናት ያግዛሉ። ከሥነ ጽሑፋዊ ዋጋቸው ባሻገር የአገሪቱን ፖለቲካዊ ታሪክ ብሎም የቤተ ክርስቲያን ፖለቲካ (ነገረ ቤተ ክርስቲያን) ለማጥናት ጠቀሜታ አላቸው። መጽሐፈ ብርሃን የኢትዮጵያን ታሪክ ለመሰነድ ፋይዳ ያለው ሲሆን ከዚያም አልፎ በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ጥናት ሚናው ትልቅ ነው። ለሃይማኖት ጥናት፣ ለሃይማኖት ክርክሮች ታሪክ፣ ለነገረ ቤተ ክርስቲያንና ሥነ መለኮታዊ ጉዳዮች ጥናትና እውቀት ሁነኛ ምንጮች ነው። በተለይ የመካከለኛውን ዘመን ማኅበረ-ፖለቲካዊና ባህላዊ አውድ ለመረዳት ዋነኛ ግብዓት ይሆናል። ለህዝብ አንድነት፣

ለሃይማኖት ውስጣዊ አንድነትና ለመንግሥቱ መጽናት ብሎም ለሃገረ መንግሥት ግንባታ እንቅስቃሴ መጽሐፉ ጉልህ ሚና ነበረው፤ ዋነኛው የተጻፈበት ዓላማም ይሄው ነበር፡፡

የመካከለኛው ዘመን ድርሰቶች ለኢትዮጵያ ጥናት መረጃ ምንጭ ሆነው ያገለግላሉ፡፡ የኢትዮጵያን የፖለቲካና የነገረ መለኮት ታሪክ ለማጥናት ሁነኛ ምንጭ ናቸው፡፡ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ታሪካዊ እና ሃይማኖታዊ የዘመኑን ሁነቶች ለመገንዘብ፣ ለግእዝ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ጥናት የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ ሃዲስ ባህላዊ፣ ኃይማኖታዊና ማኅበራዊ አቅጣጫ ጠቋሚ የትምህርት ባህልንም የቀየሱ ናቸው፡፡ የመካከለኛው ዘመን የባህልና የትምህርት የሥነ ጽሑፍ ህዳሴ የታየበት ነው ሲሆን ከነገረ መጻሕፍት ወጸሐፍት፣ ላይብረሪ ሰርቪስና ቤተ መጻሕፍት አንጻር መጠናት ይችላል፡፡ አብዛኞቹ የንጉሡ መጻሕፍቱ በወቅቱ ለተነሱ የሃይማኖት ውዝግቦች ምላሽ ይሆኑ ዘንድ የተጻፉ ናቸው፡፡ የደቂቀ እስጢፋኖስ፣ የቤተ ተክለ ሃይማኖትና የቤተ ኤዎስጣቴዎስ በሰንበት አባበር ላይ የተነሳው ክርክር፣ የቤተ አይሁድ ልዩነቶች፣ ሰባልዮሳዊነት (ከሃገር ውጪ የመጣ ከክርስቶስ ነገረ ስጋዌ አስተምህሮ ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች)፤ የዘሚካኤልና ገማልያል የሃይማት ክርክሮች በዘመኑ ከተነሱት ሃይማኖታዊ ውዝግቦች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የንጉሡ መጻሕፍት ለእነዚህ ልዩነቶች ምላሽ ለመስጠት ባቀደ ዓላማ ተዘጋጅተዋል፡፡ መጽሐፈ ብርሃን ከእነዚህ አንዱ እንደሆነ በጥናቱ ተመልክቷል፡፡ መጻሕፍትና የእውቀት ስርጭት ተጠቅሞ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት ለማጠንከር ሃይማኖታዊ መጻሕፍት በስፋት ስርጭት ላይ ውለዋል፡፡ የእውቀት መስፋፋት፤ የሃይማኖት መጻሕፍት መስፋፋት፣ የመንፈሳዊነት ማደግ፣ ጠንካራ ሃይማኖታዊ መንግስት በመመስረት ጥንታዊውን የአክሱም አቋም የማጠናከር ዓላማ ነበረው፡፡ የሃገር አንድነትን ጠንካራ መሰረት ለማስያዝ፣ አዲስ የፖለቲካና ማኅበራዊ አስተሳሰብ ለመዘርጋት ጥቅም ነበራቸው፡፡ እንደንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብ እምነት የቤተ ክርስቲያን አንድነት ሃገራዊ አንድነትን ይስባል፡፡ የመኳንንቱና መሳፍንቱ ከማዕከላዊነት የማፈንገጥን ነገር ለማስታገስ መጻሕፍቱ መመሪያን በማስረጽ ረገድ ጠቅመዋል፡፡ በዚህ ጥናት መጽሐፈ ብርሃን የያዛቸው እንደነገረ መጻሕፍት፣ አምልኮተ ባዕድ፣ ሙታንና ይቅርታ፣ ትምህርት እና ንባብ፣ ተግባረ እድ፣ የቀለም ትምህርት፣ ጸሎት ሌሎች ፖለቲካዊና ሃይኖታዊ ሃሳቦች ተዳስሰዋል፡፡

## ማጣቀሻዎች


ጌታቸው ኃይሌ:: (1997):: *የአባ ባሕርይ ድርሰቶች አሮሞችን ከሚማለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋራ*:: አዲስ አበባ::

ጌታቸው ኃይሌ:: (1999):: *የቅዱስ ያሬድ ታሪከና የግእዝ ስነ ጽሑፍ*:: አዲስ አበባ::

ጌታቸው ኃይሌ:: (2010):: *ስለ ግዕዝ ሥነ ጽሑፍ የተሰበሰቡ አንዳንድ ማስታወሻዎች::* ኒው ዮርከ:- አሳታሚ ያልተገለጸ::

አከሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ:: (1945):: *መርሀ ልቡና*:: አዲስ አበባ:- መርሐ ጥበብ ማተሚያ::

ሰሎሞን ዮሐንስ:: (2001):: *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወርቃማ ዘመናት*:: አዲስ አበባ:- ባናዊ ማተሚያ::

አምሳሉ አከሊሉ:: (1976):: *አጭር የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ*::አ.አ.ዩ- ያልታተመ::

አምሳሉ ተፈራ (ቀሲስ፣ዶ/ር):: (2011 ዓ.ም):: ነቅዐ መጻሕፍት:: አዲስ አበባ:- አሳታሚ ያልተገለጸ::

አጼ ዘርዓ ያዕቆብ:: *መጽሐፈ ብርሃን*: ህትመት:- ማኅበረ ቅዱሳን:: (2010):: ትርጉም:- አንዷለም ኤርሚያስ (ዲ/ን)

Adamu and Belaynesh. (1970). The Role of the Ethiopian Orthodox Tewahdo Church in Literature and Art. In Taddesse, and Sergew (Eds.). *The Church of Ethiopia: A Panorama of History and Spiritual Life.* (pp.45-49). Addis Ababa: B.S.P.E.

Getachew Haile. (1968). Remarks on the Content of Ge’ez Literature of Ethiopia. *History Journal, 3* (2).

___________. (1996). *Ethiopic Literature.* In Grierson Roderick (Eds.), *Africa Zion: The sacred art of Ethiopia* (pp.125-138). USA: Yale University

___________. (2013). The Homily of Zara Ya’eqob’s Mashafa Berhan on the rite of Baptism and Religious Instruction. Corpus Scriptorum Christianorum Orientalium 653-654, Scriptores Aethiopici 114-115, Lovanii: In aedibus Peeters.

Harden J.M. (1926). *An Introduction to Ethiopic Christian Literature.* London: Garland.

Hayatt, H.M. (1928). *Manuscripts and Literature: Church of Abyssinia*. London: Garland.

Kaplan, S. (1981). Hagiographies and the History of Medieval Ethiopia. *History in Africa, 1* (2).

Kinefe-Rigb Zelleke. (1975). Bibliography of the Ethiopic Hagiographical Traditions. *Journal of Ethiopian Studies, 13* (3).

Sergew Hable Selasse. (1972). *Ancient and Medieval Ethiopia to 1270.* Addis Ababa: B.S.P.E.

Taddesse Tamrat. (1970). *Hagiographies and the Reconstruction of Medieval Ethiopian History.* Addis Ababa: H.S.I.

Taddesse Tamrat. (1972). *Church and State in Ethiopia 1272-1527.* Oxford: Oxford Univ. Press